☩

# ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐይማኖት

# የቤተ ተክለ ሥላሴ ከበደ ወልደ ኢየሱስ

# አቋምና ውሳ ኔ

# ቃ ለ ጉ ባ ኤ

ኅዳር 22 ቀን 1991 ዓም
ዐ ዲ ስ ዐ በ ባ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ
አሜን

**የቤተ ተክለ ሥላሴ ከበደ ወልደየሱስ**
**የቤተሰብ ስብሰባ**
**ቃለጉባዔ**

**በስብሰባ የተገኙ**

| | |
|---|---|
| ወንድም ልደተ ወልድ ማትያስ ከበደ፤ | እህት ማኅተመ ሥላሴ አልማዝ አበበ |
| ወንድም ትርሢተ ወልድ ሴም ከበደ | እህት እህተ ማርያም አልማዝ ዮሴፍ |
| ወንድም ፍቅረ ወልድ ሰፎንያስ ከበደ | |
| ወንድም አካለ ወልድ ኢሳይያስ ከበደ | እህት ወለተሥላሴማኅደረ(አበራሽ) በላይ |

**በስብሰባ ያልተገኙ**

| | |
|---|---|
| ወንድም ሥምረተ ወልድ ዳዊት ከበደ | እህት ፀዳለ ማርያም ሐረገወይን (ታፈሰች) |
| ወንድም ሂሩተ ወልድ ን/ዕ ኤርምያስ ከበደ | እህት ሂሩተ ማርያም ራሔል ዘካርያስ |

**የስብሰባው ቀን** — እሑድ ጥቅምት 22 ቀን 1991 ዓም፤ ከቀ ኑ በ800 ሰዓት
**የስብሰባው ቦታ** — በወንድማችን ማትያስ ከበደ ቤት

**የስብሰባው ምክንያት** — **ወንድማችን ንቡረዕድ ኤርምያስ ከበደ ባቀረበው የሃይማኖትና የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጥያቄ ላይ ተወያይቶ ለመወሰን፤**

ስብሰባው በፀሎት ተጀምሯል።

በወንድማችን ንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ ጥያቄ ጥቅምት 10 ቀን 1991 ዓም ከቀ ኑ በ1100 ሰዓት ላይ ወንድም ዳዊት ከበደና እህት ራሔል ዘካርያስ ጭምር በተገኙበት በተካሄደው ስብሰባ ላይ፤

ወንድም ንቡረዕድ ኤርምያስ ከበደ ቀደም ሲል" የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ነት ተዋኅዶ ሃይማኖት" በሚል ስያሜ የተለያዩ ጽሑፎችን በወንድም ዳዊት ከበደ በኩል እየላከ እንድናውቅ ማድረጉን፤ ቀጥሎም ካሁን በፊት ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ መጥቶ በ ነበረበት ወቅት ስለዚሁ ጉዳይ በስብሰባ ያ ነጋገረን መሆ ኑን፤ ስለ ልጁ ዶክተር ትምህርተ ኤርምያስ ጋብቻ ጉዳይ እና ከላይ የተጠቀሰውን ሃይማኖት በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ ፈተናና ትግል ያሳለፈና ለወደፊቱም በኢትዮጵያ ውስጥ ከቤተሰቡ ጀምሮ የስብከት ትምህርቱን ለመቀጠል ከ ነባለቤቱ ወደአገሩ ተጠቃልሎ መመለሱን፤ በዚህም በጀመረው የቅዱሱ ኪዳን እም ነት ላይ ምንም ዓይ ነት ድርድርም ሆ ነ ውይይት የማይቀበል መሆ ኑን፤ይህንን የቅዱሱ ኪዳን ተዋህዶ ሃይማኖት የሚያጠናክርና የጎደለውን የሚያሟላ አስተያየት ካልሆ ነ በቀር፤ የእም ነቱን ዓላማ የሚያናጋ ወይም የሚለውጥ ሀሳብ ወይም አቋም እንደማይቀበል በውሳ ኔ አጠንክሮ ከገለፀ በኋላ፤ ቤተሰቡ የእም ነቱ ተከታይ መሆን ወይም አለመሆ ኑን ብቻ ለይቶ አቋሙን እንዲገለጽለት ጠይቋል።

ከዚህም በማያያዝ ዕድሜውን ሙሉ በጀመረው በዚህ የሃይማኖት ተጋድሎ እስከመጨረሻው ድረስ የሚገፋበት ከመሆ ኑም በላይ፤ በዚህ የቅዱስ ኪዳን ሃይማኖት አብረውት ከማይሄዱት ጋር የ ነበረውን የዝምድናም ሆ ነ የወዳጅ ነት ግንኙ ነት ጨርሶ የሚያቋርጥ መሆ ኑን አበክሮ በማስረዳት፤ የቅዱሱን ኪዳን የሃይማኖት፤ የምስጋና፤ የፀሎትና የቃልኪዳን ምስክር ነት ግዴታ መግቢያ ጽሑፍ ጭምር በዝርዝር ለስብሰባው በንባብ አሰምቷል። በመጨረሻም " በዚህ ሃይማኖት ከተለያየን በመካከላችን ምንም ዓይ ነት ዝምድና ወይም የወዳጅ ነት ግንኙ ነት አይኖርም "የሚል

መስከረም 16 ቀን 1990 ዓም የተፃፈና በወንድም ንቡረ ዕድ ኤርምያስና በእህት ራሔል የተፈረመ መልዕክት በየእጃችን ታድሎናል።

በወንድም ንቡረዕድ ኤርምያስ የተሰጠው ገለፃ ከሁለት ሰዓት በላይ የፈጀ በመሆ ኑና ውይይቱን በዕለቱ ለመቀጠል ጊዜውም ስለመሸ የሚቀጥለው ስብሰባ ለእሑድ ጥቅምት 22 ቀን 1991 ዓም ከቀ ኑ በ800 ሰዓት በዚሁ ቦታ ስብሰባው እንዲቀጥል ተቀጥሮ የዕለቱ ስብሰባ አበቃ።

## ሁለተኛ ስብሰባ

እሑድ ጥቅምት 22 ቀን 1991 ዓም ከቀ ኑ በ800 ሰዓት የተቀጠረው ስብሰባ ከመጀመሩ በፊት ወንድም ዳዊት ከበደና እህት ሐረገወይን (ታፈሰች)፤ ወንድም ንቡረዕድ ኤርምያስ ከበደና እህት ራሔል ዘካርያስ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ድረስ ተጠብቀው ባለመምጣታቸው በተገኙት አባላት ውይይቱ እንዲቀጥል ጉባዔው ተስማምቶ ስብሰባው በፀሎት ተከፍቷል።

በቅድሚያ እንደተለመደው የስብሰባው ቦታ ወላጆቻችን በ ነበሩበትና ሁላችንም ተወልደን ባደግንበት ቦታ ላይ በታላቅ ወንድማችን ማትያስ ከበደ ቤት መሆ ኑ ቀደም ብሎ ቢታወቅም፤ ወንድም ንቡረዕድ ኤርምያስ ሀሳቡን በመለወጥ ስብሰባው በራሱ ቤት እንዲቀጥል ወንድም ማትያስን በስልክ ስለጠየቀ፤እንደቤቱ ሥርዓት በተጀመረበት ቦታ መቀጠል እንዳለበት የተ ነገረው መሆ ኑ ተገልጿል።

ቀጥሎም ሐምሌ 7 ቀን 1990 እና መስከረም 16 ቀን 1991ዓም የተጻፉ የወንድም ንቡረዕድ ኤርምያስ ሁለት መልዕክቶች በንባብ እንዲሰሙና ቀደም ሲል በወንድም ዳዊት አሳሳቢ ነትና በርሱው አማካይ ነት እየቀረቡ የተ ነበቡት ጽሑፎች ጭምር ውይይት እንዲደረግባቸው ጉባዔው ተስማምቶ፤ እያንዳንዱ አባል አስተያየቱን ሰጥቶበታል።

## የተደረጉ ውይይቶችና የተሰጡ አስተያየቶች

የቤተሰባችን አቋም ከጥንት አያት - ቅድምአያቶቻችን ጀምሮ በክህ ነት አገልግሎት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፤ዕም ነቱም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኀዶ ሃይማኖት (ወልድ ዋህድ) የወጣ አለመሆ ኑ፤እኛም በሕይወት ያለ ነው ልጆቻቸው ይህን ኑ ሃይማኖታችንን ተረክበን በክህ ነት ጭምር ስናገለግል የቆየን ከመሆ ኑም በላይ፤ ለልጅ ልጆቻችንም ይህች ኑ የቀናችና የፀናች ሃይማኖት በማስተማር እያስተላለፍን መሆ ኑ፤ ወንድማችን ንቡረዕድ ኤርምያስ ከልጅ ነት ዕድሜው አንስቶ የ ነበረው ምኞትና ዝንባሌ እንዳሁን ጎልቶ ሳይታይ፤ መጀመሪያ በዲቁና ከዚያም በዚችው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኀዶ ሃይማኖት ሥርዓትና ሕግ የቅስና ማዕረግ ተቀብሎ ሲያገለግል መቆየቱ፤ በጠቅላይ ቤተ ክህ ነት መ/ቤትም ከክፍል ሹም ነት እስከ ዋና ሥራ አስኪያጅ ነትና አልፎም የጥንታዊት አክሱም ንቡረ ዕድ ነት ማዕረግ መድረሱ፤ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመ ነ መንግሥት መጨረሻ ላይ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ሆኖ ሣለ፤ እንደሌሎቹ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በደርግ አገዛዝ ሰባት ዓመት ታስሮ መቆየቱና እዚያም በ ነበረበት ጊዜ በእሥር ቤት ውስጥ እየቀደሰ ሥጋ ወደሙ ያቀብል እንደ ነበረ ካንደበቱ መስማቱ፤ እዚያ ሣለ ያዘጋጀውም መጽሐፍ ከትምህርተ መለኮት አንጻር ሥጋዊን ከመንፈሳዊ ቀላቅሎ የያዘ በመሆ ኑ በሊቃውንት ጉባዔ ታይቶ ውድቅ መደረጉ፤ ወደ አሜሪካ ከሄደ በኋላም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኀዶ ሃይማኖት ውጭ በተለየ ስያሜ አዲስ ሃይማኖት በማቋቋም፤ፀንቶ ከቆየው ትምህርተ ሃይማኖትና ስርዓተ ቤተ ክርስቲያን የተለየ ስርዓት ሲፈጽምና ሲያስፈጽም የ ነበረ ለመሆ ኑ በየጊዜው ከሚልካቸው ጽሑፎች ማወቅ መቻሉ፤አዲስ የመሠረተውን የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖት የሚቀበሉት ተከታዮች ሁሉ፤የቃል ኪዳን ምስክር ነታቸውን በጉባዔ ፊት እንዲሰጡና መተማመኛ ቅጽ እንዲፈርሙ የሚያስገድድ ስለመሆ ኑ ከሰጠው መግለጫ መረዳት ተችሏል።

እኛ ከአባቶቻችን አንበልጥምና ጉዳዩ ለቤተሰብ ይቅረብ ወይም በሊቃውንት አባቶች ይታይ የሚል ሀሳብ ሲቀርብለት " እ ኔን የሚመራኝ መንፈስ ነው " በማለት ምክርና አስተያየት ለመቀበል

ፈቃደኛ አለመሆ ኑ፤ጥንታዊት ርትዕት ሃይማኖታችን በትምህርተ ሃይማኖት እና በሥርዓተ ቤተክርስቲያን የተሟላች መሆኗ እየታወቀ፤ ምንም መመሪያ የሌላት በማስመሰልና መጻሕፍትን ለራሱ እንደሚመቸው በመተርጎም ፀሎተ ሃይማኖትን፤ አቡ ነ ዘበሰማያትንና በሰላመ ገብርኤልን በማሻሻልና በማስፋፋት እንደአዲስ ፀሎት አዘጋጅቶ ማቅረቡ፤ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪ ሲደረግለት ባለመ ቀበል ከቤተ ክርስቲያ ኒቱ ተለይቶ በቅብዓ ሜሮን ባልከበረና ታቦት በሌለበት ቦታ ከቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ውጭ ቅዱስ ቁርባን እያዘጋጀ የሚያቀብል መሆ ኑ፤በአሜሪካን አገር በሚሰጠው የክህ ነት አገልግሎት ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን የማይወክል ስለመሆ ኑ ከቅዱስ ሲኖዶስ ውሳ ኔ የተላለፈ መሆ ኑ፤ ቅዱሳን አበው በመንፈስ ቅዱስ መሪ ነት ጽፈው ያኖሩልንንና የኢትቶጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በመመሪያ ነት ተቀብላ ስትሠራበት የኖረቹውን ፍትሐ ነገሥት " ሰው ሠራሽ " በማለት መንቀፉ፤ በየጊዜው በሚያዘጋጃቸው ጽሁፎቹ ላይ ይህን " የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ነት ተዋህዶ" በሚል አዲስ ስያሜ ያቋቋመውን ሃይማኖት የማይቀበል ሁሉ በርሱ ዘንድ ኢትዮጵያዊ አለመሆ ኑን በአፅንኦት አስምሮበታል።

ወደኋላ መለስ ብለን ሁ ኔታውን ስንመለከት ሥልጣ ነ ክህ ነት ከተቀበለ አንስቶ የቆየውን ያባቶቻችንን ሃይማኖታዊ ባህልና ሕግ ለመጣስ ባለው ጽ ኑ ፍላጎት ፤ ቀሳውስት አባቶቻችን ሲጠሩበት የኖሩትን "መምሬ "የሚለውን ስም በመናቅ፤ ከሌሎች ባዕዳን አብያተ ክርስቲያናት ካህናት ጋር የሚያጎዳኘውን "ቄስ" የሚለውን መጠሪያ ስም መምረጡና ለጥንታዊ ነቻችንና ለታሪካችን ሕያው ምልክት ሆኖ የቆየውን የሻሽ ጥምጥም ትቶ በቅብዓ ክህ ነት የከበረውን ራሱን እንደሕዝባዊ ተጋልጦ መታየቱ፤ በሕገ ቤተ ክርስቲያናችን ሥልጣ ነ ክህ ነት የሚሰጠው ብቃት ላላቸው ወንዶች ብቻ ሆኖ ሣለ፤በየጽሑፉና ገለፃው ላይ" እ ኔና ባለቤቴ በተቀበል ነው ሥልጣ ነ ክህ ነት " ማለቱ፤ "እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ማንም አይለየው " የሚለውን የጌታ ቃል በመጣስ በስርዓተ ተክሊል፤ በቃል ኪዳንና በቅዱስ ቁርባን የተፈፀመውን የገዛ ልጁን ጋብቻ፤ ሕጋዊ መሠረት ነት በሌለውና ባልተረጋገጠ ጉዳይ በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንደተፈፀመ በማስመሰል ጋብቻው እንዲፈርስ ውሳ ኔ መስጠቱ፤በአንፃሩም ቀደም ሲል የወንድም ሰፎንያስ ልጅ- የመና ጋብቻ "በቁርባን አልተፈፀመምና አልተቀበል ነውም " በማ ለት ጋብቻውን ለማፍረስ መሞከሩ በጋብቻ ሥርዓት ላይ ያለውን የተዛባ አመለካከት ያጎላው ሲሆን፤ እራሱን ከመንፈሳዊና ከሥጋዊ ሕግ በላይ ማድረጉን ይበልጥ ማስገንዘብ ችሏል።

በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳ ኔና· በራሱ ፍላጎትም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መለየቱ በግልጽ እየታወቀ፤ አዲስ አበባ መጥቶ በቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ቀድሶ ማቁረቡ ማናለብኝ ነትና ድፍረት መሆ ኑ፤ቅዱሱ ኪዳን በሚል ስያሜ የፈጠረው ሃይማኖት አዲስ መሆ ኑ እየታወቀ፤በጽሑፎቹም ሆ ነ በገለፃው ላይ " ጥንታዊት የአባቶቻችን ሃይማኖት " እየተባለ መጠቀሱ በቆየው ሃይማኖታችን ፀንተው ያሉትን ምዕመናን በማስመሰል ለማሳሳት የሚጠቀምበት ዘዴ መሆ ኑ፤ እንዲሁም ለቤተሰቡ ጉባዔ የእም ነት አቋሙን በገለፀ ማግሥት በዚሁ ላይ ለመወያየት ከቤተሰቡ ጋር ቀጠሮ ይዞ ሣለ፤በመካከሉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት በተመሰረተው የቅዱስ ቂርቆስ ማኅበር ስብሰባ ላይ አባላቱ የዓላማው ተከታይ እንዲሆ ኑት መቀስቀሱና ትምህርቱን ያለቦታው በግል መኖሪያ ቤቱ በኅቡዕ ለመስጠት መጋበዙ የሃይማኖት ድርጅቱን ለማስተዋወቅና የማኅበሩን አንድ ነት ለመከፋፈል ሆን ብሎ ያደረገው መሆ ኑን ያስረዳል።

ሐምሌ 7 ቀን 1990 ዓም በፃፈው መልዕክቱ ላይ በልጅ ነት እድሜው ክህ ነት ለመቀበል አባታችንን ጠይቆ፤ "አይሆንም " መባሉንና እርሱ ከሞተ በኋላ ግን ከሌሎቹ ይልቅ እርሱ ተመርጦ ቅስና ለመቀበል መቻሉን መግለፁ፤ ካሁን ቀደም ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በ ነበረበት ወቅት በተካሄደው የቤተሰብ ውይይት ላይ ይህንን አዲስ ክስተት በወቅቱ በግንባር ከመቃወም አንስቶ በወንድም ዳዊት አማካይ ነት በየጊዜው የሚመጣውን የጽሑፍ መልእክት በማዳመጥ ተቃውሟችንን በዝምታ ከማሳየት በቀር በጋራ የተሰጠ አንዳችም መልስ አለመኖሩ፤ በየጊዜው በሚልካቸው ጽሑፎቹ ላይም ሆ ነ በቃል ገለፃው ላይ ቤተሰቡ በዚሁ ቅዱሱ ኪዳን በሚለው በርሱ እም ነት ፀንቶ እንደሚገኝና ደጋፊ እንደሆ ነ ማስመሰሉና እ ነዚህን የመሳሰሉት

በርሱ በኩል በጽሑፍም በቃልም የተገለጹ ፍሬ ሃሣቦች ተ ነስተው ጉባዔው አንድ በአንድ በጥልቀት ተ ነጋግሮባቸዋል።

በመሰረቱ ከጥንት ሲያያዝ እንደመጣው፤የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ቤት የሕይወቱ መሠረትና መመሪያ መሆ ኑ እየታወቀ ፤ ከዚህ ቤተሰብ፤ ያውም የክህ ነት ሥልጣን ከተቀበለው ወንድማችን ይህንን የመሰለ ንፋቄ መ ነሳቱ ቤተሰቡን እጅግ አሳዝኗል፤አስደንግጧልም። ነገሩ በገሃድ ገፍቶ በዚህ የሃይማኖት ጉዳይ ላይ ቤተሰቡ ሚናውን እንዲለይ በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በቃል ጭምር በግንባር በድፍረት መጠየቁ ቤተሰቡን ፈተና ላይ ጥሎታል። አልፎ ተርፎም በቅዱስ ቂርቆስ ማኅበር ላይም ይኸው ጥያቄ በይፋ ቀርቦ ምስጢሩ ገሃድ ወጥቷል። አሁን ጉዳዩ ይፋ በመውጣቱ እንደቀድሞው በዝምታ ማለፍ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ስለደረሰ ቤተሰቡ የበኩሉን አቋም ማሳወቅ እንዳለበት አምኖበታል።

## የቤተሰቡ አቋምና ውሳ ኔ

አንደኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ነት ተዋሕዶ ሃይማኖት የሚለውን በተመለከተ

ቅዱሱ ኪዳን ለሚለው፤ የሰባቱ ኪዳናተ አበው መደምደሚያ ርዕስ የሆ ነው ነቢያት የተናገሩለት፤ ሐዋርያት ሊቃውንት የመሰከሩለት፤"--- ከዚህ ሕዝብ ጋር አዲስ የምገባው ቃል ኪዳን አለ፤" ብሎ ጌታ ተስፋ የሰጠው አዲስ ኪዳን ....". **ወንጌል** ..." ነው።

በቤተሰቡ ዕም ነት ከሃይማኖታቸው ሳይናወጡ እንደ እኛ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ፀንተው የኖሩ ምዕመናን በዐርባና በሰማንያ ቀን ተጠምቀው የሥላሴን ልጅ ነት ባገኙ ጊዜ በክርስትና አባቶቻቸውና እናቶቻቸው አማካይ ነት በመሃላ ከተቀበሉትና ከክርስቶስ ጋር ከገቡት አዲስ ቃል ኪዳን ከሆ ነው ከወንጌል በቀር ሌላ ቃል ኪዳን መግባት አያስፈልጋቸውም።

ሃይማኖት ለለወጡም ቢሆን የክርስትና ጥምቀት እንደገና መጠመቅ ሳያስፈልጋቸው ቄደር የሚባለውን የንስሃ ጥምቀት ተጠምቀው የሚታደሱበት ሥርዓት ስላለ በዚያው መሰረት ብቻ የሚፈፀም ነው። የክርስትና ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ ነውና።

ኢትዮጵያዊ ነት ለሚለው ፤ይህ ስም ክርስቲያናዊ ነት ወይም ክርስትና የሚለውን ተክቶ የገባ ሆኖ ይታያል። ነገር ግን ይህ ኢትዮጵያዊ ነት የሚለው የዜግ ነት ስም እንጂ የቤተ ክርስቲያን መሥራችና የዓለም ቤዛ ከሆ ነው ከክርስቶስ ጋር የሚያዋህድ፤ የሚያዛምድ ስላልሆ ነ በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልንበትን ስም ሊተካ አይችልም።

ኦርቶዶክስ ስለሚለው ቃል፤ የአባቶቻችን ሃይማኖት ነው በማለት" ኦርቶዶክስ "ለሚለው ቃል የተዛባ ትርጉም በመስጠት ይህ ነባር የሃይማኖት ስም ከቦታው ተሰርዞ እንዲወጣ ተደርጓል። ይህም ሃይማኖት ከአባቶቻችን የተለየ ሕፁፅ ሃይማኖት መሆ ኑን በጉልህ የሚያስረዳ ነው። በመሰረቱ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስረዳው "ኦርቶዶክስ" የሚለው ስም በ325 ዓም በ ኒቂያ መጀመሪያ የተሰበሰቡት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ከአርዮሳውያን ተለይተው የሚታወቁበት የጉባዔያቸውም የሃይማኖታቸውም ስም ነው። ይህም ከጥንቱ የግሪክ ቋንቋ ከፅርእ የመጣ ጥሬ ቃል ሲሆን በግዕዝ ርትዕት ሆይማኖት ወይም በአማርኛ የቀናች- የፀናች ሃይማኖት ማለት ነው። ተከታዮቹም ኦርቶዶክሳውያን ወይም ርቱዓ ነ ሃይማኖት( ሃይማታቸው የቀና) ይባላል።

ተዋሕዶ የሚለው ስም ደግሞ በ431 ዓም በኤፌሶን የተሰበሰቡ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ፤ ከሁለት ባሕርይ ባዮች ከንስጥሮሣውያንና ከልዮናውያን (መለካውያን) ተለይተው የሚታወቁበት፤ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ በሚል ዕም ነት የፀ ኑ መሆናቸው የሚገለጽበት የጉባዔ ያቸውና የሃይማኖታቸው ስም ነው።
ስለዚህ ቤተ ክርስቲያናችን በሦስቱ የመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን ጉባዔያት ማለትም በ ኒቂያ፤ በቁስጥንጥንያና በኤፌሶን የተወሰ ነውን ትምህርተ ሃይማኖትና ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ብቻ

የተቀበለች እንደመሆኗ፤በዚሁ ፀንታ የመኖሯ ማረጋገጫ የሆ ነውን “ ኦርቶዶክስ - ተዋሕዶ” የሚለውን ጣምራ ስም የሃይማኖቷ መጠሪያ አድርጋ ይዛ ኖራለች። የአባቶቻችንም ሃይማኖት ከዚህ የተለየ መጠሪያ ስም አል ነበረውም ፤ የለውምም።

በተጨማሪም” ኦርቶዶክስ” የሚለው የሃይማኖት ስም ከፅርእ ቋንቋ የተወረሰ ጥሬ ቃል በመሆ ኑ ብቻ የሌሎች የሃይማኖት ጥገኛ እንሆን ዘንድ በግድ የተጫ ነብን ባዕድ ስያሜ ነው ተብሏል። ታድያ እንዲህ ከሆ ነ ከፅርእ ቋንቋ የተወረሱ ቃላት ብዙዎች ናቸው። ይልቁንም እኛን ክርስቲያን ያሰኘን “ክርስቶስ” የሚለው የአምላካችን ስመ-ሥጋዌው ከዚያው ከፅርእ የመጣ ውርስ ቃል እንደመሆ ኑ፤ ይህሣ ምን ሊባል ይሆን ?

ሁለተኛ “ <u>ቤተ ክርስቲያናችን ከማንም የተለየች ብቸኛ ናት “ ለተባለው</u>፤

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን እግዚአብሔርን በማወቅና በአምልኮቱ ፀንቶ በመኖር ታሪኳ ከማንም ቀዳሚ ነት ያላት ጥንታዊት ስለሆ ነች በዚህ ረገድ ማንም ተፎካካሪም ተወዳዳሪም እንደሌላት የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ ከክርስትና ወዲህ ልዩ ነቷ ከአርዮሳውያን፤ ከሁለት ባህርይ ባዮችና ከቡርስታንቶች ጋር እንጂ፤ በትምህርተ ሃይማኖትና በቀኖና ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያዎቹ ሦስቱ የቤተ ክርስቲያን ጉባዔያት የተወሰ ነውን ከሚቀበሉ አራቱ አብያተ ክርስቲያናት ማለት ከእስክንድርያ፤ ከሦርያ፤ ከአርማንያና ከህንድ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ጋር “… ወልድ ዋሕድ ..” በማለት አንድ ናት፤ ልዩ ነት የላትም።

ሦስተኛ <u>“ የአባቶቻችን ሃይማኖት ነው” እየተባለ የሚሰበከውን በተመለከተ፤</u>

ይህ የተባለው ሃይማኖት ውስጠ ምስጢሩንና ዓላማውን በሚገባ ጠልቀው ያልተረዱ ወገኖችን በለዘበ ፈሊጣዊ አቀራበብና አ ነጋገር እጅ ለማድረግ ሲባል ፤ ከላይ በአፍኣ የአባቶቻችንን ስም ቀብቶና “ ተዋሕዶ” የሚለውን ስም በቁንጽል አስገብቶ በመቅረቡ ብቻ የአባቶቻችን ሃይማኖት ሊሆን አይችልም።

አራተኛ ..” <u>ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ..”የተባለውን በተመለከተ</u>፤

ጌታ በወንጌል እንደ ነገረን፤ ሃዋርያትም የርሱን ቃል መሰረት አድርገው እንዳስተማሩን የእግዚአብሔር መንግሥት ሰማያዊት (ላዕላዊት) ስለሆ ነች..” መንግሥተ ሰማያት..” በመባል ትታወቃለች። በመንግሥተ ሰማያት አንፃርም <u>በዚህ ዓለም ያለችው የእግዚአብሔር መንግሥት ቤተ ክርስቲያን ናት</u>። ይህችውም ለእግዚአብሔር መንግሥት መንትያዋ አምሳያዋ ስለሆ ነች በቦታና ጊዜ አትወሰንም። ኢትዮጵያ ግን በተወሰ ነ ክልል ያለች ውሱን አገር ስትሆን፤” ሀገረ-እግዚአብሔር” ብትባል እንጂ ምልዕት -ስፍሕት ለሆ ነች ለእግዚአብሔር መንግሥት መጠኗም አምሳያዋም ልትሆን አትችልም።

የእግዚአብሔር መንግሥት የሆ ነችው የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን መላእክት ከተፈጠሩ በኋላ በዓለመ መላእክት ተመሠረተች። የመላእክት የተፈጥሮ ጓደኛቸው የ ነበረው ሣጥናኤል በዚያች ሰማያዊት ቤተ ክርስቲያን ላይ አምፆ በተ ነሳ ጊዜ ባልንጀሮቹ መላእክትን የክህደቱ ተባባሪ ለማድረግ ሞክሮ ሳይሣካለት በመቅረቱ ተወግዞና ከማዕረጉ ተዋርዶ ተጥሏል።

በሣጥናኤል ምትክ አዳም ከተፈጠረ በኋላ ሁለተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን በገ ነት ተመሠረተች። እርሱም አውራ ጠላቱና የክህደት መምህር በሆ ነው በሣጥናኤል ስብከት ተታልሎ የፈጣሪውን ትዕዛዝ በማፍረሱ ከክብሩ ተዋርዶ በሥጋው ምድረ ፋይድ፤ በ ነፍሱ ሲዖል እንዲወርድ ተፈረደበት። ይሁን እንጂ በበደሉ ተጸፅቶ የፈጣሪውን ገፀ ምሕረት በንስሃ ስለፈለገ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ሊያድ ነው ፍጹም ተስፋን ሰጥቶታል።

እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም ከቅድስት ድንግል እመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከ ነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው በሆ ነ ጊዜ ሦስተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ጴጥሮስ መሠረት ነት በመቶዛያው ቤተሰብ በዚህ ዓለም ተመሠረተች። መሥራቿ፣ ገገርዋና መሪዋም ራሱ ባለቤቱ ነው።የዚች ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ የወንጌል ካህናት ከሆ ኑት ሃዋርያት መካከል በክህደቱ ተወግዞ የተለየው የመጀመሪያው መናፍቅ አስቆረታዊው ይሁዳ ነው።

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ቤተ ክርስቲያን በሰማይም በምድርም በዓለሙ ሁሉ ምልዕት የምትባለውም ስለዚህ ነውና ኢትዮጵያን የቤተ ክርስቲያን ምትክ አድርጎ የእግዚአብሔር መንግሥት ብሎ መሰየም ምልዕት ስፍሕት የሆ ነችውን የእግዚአብሔር መንግስት በቦታ መወሰን ይሆናል።

አምስተኛ "<u>ፍትሐ ነገሥት" የተባለውን የቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት በተመለከተ</u>

ፍትሐ ነገሥት የሚባለው የቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መጽሐፍ፣"ጊዜ ያለፈበትና ሰው ሠራሽ ስለሆ ነ ተቀባይ ነት የለውም "ተብሏል። ይሁን እንጂ ይህንን መጽሐፍ በመንፈስ ቅዱስ መሪ ነት የደረሱትና ያዘጋጁት በ ኒቅያ የተሰበሰቡ ሠለስቱ ምዕት መሆናቸውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል። ይህንንም መጽሐፍ ሲያዘጋጁ መ ነሻና መሠረት ያደረጉት ፣ለፀሎተ ሃይማኖት ዝግጅት አመክንዮተ ሐዋርያትን መሠረት እንዳደረጉ ሁሉ፣ ቅዱሳን ሐዋርያት በ51 ዓም በኢየሩሣሌም የመጀመሪያውን ጉባዔ ባደረጉ ጊዜ ፣ጌታ ከትንሣኤው በኋላ እስከ ዕርገቱ ያስተማረውን መጽሐፈ ኪዳን እንደ መሠረት ድንጋይ አድርገው የጻፉትን ግጽው፣ ሥርዓተ ጽዮን፣ትዕዛዝና አብጥሊስ የተባሉትን አራቱን ሲኖዶስ፣43 አንቀጽ ያለውን ዲድስቅልያ ና በፀሐፊው ስም "ቀሌምንጦስ" የተባለውን መጽሐፍ ነው።
ቤተ ክርስቲያናችንም በሦስቱ ጉባዔያት የተወሰ ነውን ትምህርተ ሃይማኖትና ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተቀበለች እንደመሆኗ፣ ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ለመንፈሳዊ አገልግሎቷም ሆ ነ ለአስተዳደሯ ቋሚ መመሪያዋ አድርጋ ስትሠራበት ኖራለች። ስለዚህ ወንድማችን ራሱ ለመሠረተው አዲስ ሃይማኖት መመሪያ ይሆ ነኛል በማለት ለርሱ እንደሚያመቸው አድርጎ ላሰናዳው የፈጠራ- ሕግ፣ መንገድ ለመጥረግ ሲል ፀንቶ የቆየውን ይህን የቤተ ክርስቲያን ሕግ "ሰው ሠራሽ ነው" ማለቱ፣ ራሱ ለዚህ ሥልጣ ነ ክህ ነት የበቃበትን ሕ ግ መካዱን በጉልህ ያስረዳል። ይህም ከላይ ሆኖ በሥሩ ያለውን የቆመበትን ዛፍ እንደሚቆርጥ ሰው ያስመስለዋል።

ስድስተኛ <u>ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ</u>

1ኛ በፍትሐ ነገሥት በመጀመሪያው አንቀጽ እንደተደ ነገገው፣ ታቦት ከሌለ ቤተ ክርስቲያን የለም። ቤተ ክርስቲያን ከሌለም ሥጋ ወደሙ ማክበር - መለወጥ ፣ ቀድሶ ማቁረብ አይኖርም። በቤተ ክርስቲያን መሰብሰብ በማይቻልበት ጊዜ በቤቱ ቀድሶ ማቁረብ የተፈቀደለት ኤጲስቆጶስ ብቻ ነው። ከኤጲስቆጶስ ቤት ታቦት አይታጣምና ። ያም ቢሆን በዘመ ነ አላውያን እንጂ በዘመ ነ ክርስቲያንስ በቅብዓ ሜሮን በከበረና ታቦት ባለበት ቤተ ክርስቲያን ነው እንጂ፣ ከዚህ ውጭ ሥርዓተ ቁርባን መፈፀም አጥብቆ የተከለከለ ነው። ታቦትና ቤተ ክርስቲያን በቅብዓ ሜሮን የማክበር ሥልጣን ያለው ደግሞ የኤጲስቆጶስ ወይም የቆሞስ ነት ማዕረግ ያለው ካህን ብቻ ነው። ማንኛውንም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መፈፀም በማይቻልበት ጊዜ ግን በተወሰ ነ ቦታ ሆኖ ዳዊትና አቡ ነ-ዘበሰማያት እየደገሙና ምህላ እያደረሱ እግዚአብሔርን ደጅ በመጥናት መወሰን እንደሚገባ ተደንግጓል። አንድ ካህን ከዚህ ሕግ ውጭ ማንኛውንም ሥርዓተ ምስጢር ፈጽሞ ቢገኝ ከሹመቱ እንዲሻር፣ ከምዕመናንም አንድ ነት እንዲለይ ተወስኗል።

2ኛ "በንስሃ በተመለሰ ካህን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መፈፀም ይቻላል" ለተባለው፣በፍትሐ ነገሥቱ ስለ ክህ ነት በሚደ ነግገው አንቀጽ እንደተወሰ ነው፣ ክህ ነት አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ማዕረግ ሲሆን ሚስት የደጋገመ ወይም በራሱም ሆ ነ በሚስቱ የዝሙት ነውር የተገኘበት ከሆ ነ በንስሃ የኃጢአት ሥርየት ቢያገኝም ቅሉ፣ እንደ ሕዝባዊ እንጂ ወደ ቀደመ የክህ ነት ማዕረጉ ወይም ሥልጣ ኑ መመለስ አይችልም። በሕገ ቤተ ክርስቲያናችን መሰረት ክህ ነት የሚሰጠው ብቃት ላላቸውና ሕጋቸውን ጠብቀው ባንዲት ሚስት ለተወሰ ኑ ወንዶች ብቻ መሆ ኑ

እየታወቀ፤ሥልጣነ ክህነት ለሚስትም በጋራ እንደሚሰጥ በማስመሰል "... ከልጅነት ዕድሜአችን ጀምሮ በተቀበል ነው ሥልጣነ ክህነት..." በማለት መገለጹ ፤ፀንቶ የቆየውን የቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት በማናለብኝነት ለመናድ ያለውን ቁርጠኛነት በጉልህ ከሚያሳዩ ሕገ ወጥ ድርጊቶቹ አንዱ ሆኖ ተገኝቷል።

3ኛ <u>የትምህርተን ጋብቻ</u> በተመለከተ በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንደተፈፀመ ተደርጎ "የምትሐት ሠርግ" በማለት ጋብቻው እንዲፈርስ በወላጆቿ በኩል ተወስኖል። በመሰረቱ ጋብቻው በሥርዓተ ተክሊል በመሃላ የተፈፀመና በቁርባን የታተመ ጋብቻ እንደመሆኑ፤በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት ሊፈርስ የሚችለው ከጋብቻው በፊት የቀደመ ጋብቻ መኖሩ ወይም ከጋብቻው በኋላ ዝሙት የተፈፀመ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው። የቀደመ ጋብቻ አለ እንዳይባል ፤ለአቶ ግርማ ልጅ ወለድኩ የምትል ሴት መኖሯ ከመታወቁ በቀር፤ ከርሷ ጋር የተፈፀመ ጋብቻ እንዳለ በሕግ አልተረጋገጠም። ከጋብቻው በፊት የተወለደ ልጅ ስለመኖሩም ከሠርጉ ቀደም ብሎ፤ራሷ ትምህርተ አውቃውና ይህንኑ ተቀብላ ጋብቻው መፈፀሙን የንስሃ አባታቸው ባሉበት በቤተሰቡ ፊት ሁለቱም ተማምነውበታል። ብሔራዊም ሆነ መንፈሳዊ ጋብቻ እንዲፈርስ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ያለው ደግሞ የሕግ አካል ብቻ ነው። ወላጆች ጋብቻ እንዲፈፀም ፈቃድ ከመስጠት በቀር ጋብቻ እንዲፈርስ ለመወሰን እንኳንስ እነርሱ ተጋቢዎችም ቢሆኑ አይችሉም። ይህ ጋብቻ እንዲፈርስ የሚያደርግ በቂ ምክንያት ስላልተገኘ ጋብቻው መፍረስ እንደሌለበት ቤተሰቡ የበኩሉን ሀሳብና ምክር በጊዜው ሰጥቷል። ስለዚህ ጋብቻው እንዲፈርስ በወላጆቿም ሆነ በርሷ የተሰጠውን ውሳኔ ቤተሰቡ ከሕግ ውጭ ነው ባይ ነው።

ሰባተኛ "<u>ሥልጣነ ክህነት እንዳልቀበል በአባቴ በኩል አይሆንም ተብዬ ነበር"</u> የሚለውን በተመለከተ፤

ይህ ዕውነት ከሆነ አባታችን ምናልባት ልጁ በንግግርና በጽሕፈት፤ በድርጊትም ያሳየው የነበረውን አዝማሚያ በመመልከት ይኸው እያደገ ሄዶ ዛሬ ከምናየው አስጊ ደረጃ ከመድረሱ በፊት ከወዲሁ ለመግታትና ልጁ በነፍስ ሊደርስበት ከሚችል ክፉ ነገር ለማዳን እንደ አባት ነቱም እንደ ካህን ነቱም በቅን ልቦና አስቦ ያደረገው እንደሆን እንጂ ሌላ ምክንያት ይኖራል ተብሎ አይታሰብም። ይህማ ባይሆን በእግሩ የሚተካ ልጅ ቢያገኝ የሚጠላ አባት አለን? ወይስ ስሙን በደገኛው ነቢይ ስም ኤርምያስ ብሎ መጥራቱ ለልጁ በጎ የማይመኝ አባት ሆኖ ነውን? አይደለም። በእውነቱ ለሩቅ ዓላማው ማስፈፀሚያ መሣሪያው አድርጉ ሊጠቀምበት ያሰበውንና የተመኘውን ካገኘ ዘንድ ይህንን የንጓለትን ማዕርገ ክህነት ለማግኘት ያባታችን በሞት መለየት የበጀው መሆኑን በሚያሳይ አገላለጽ በሞተ በዐርባ ዘመኑ ስሙን በማንሣት ለትውልድ በሚተላለፍ ጽሑፍ መውቀስና መክሰስ ባልተገባው ነበር። ስለዚህ ለኛ ለልጆቹ መልካም ምሳሌነት ባለው በጎ ምግባሩ በሰው ሁሉ ዘንድ የታወቀና መከበሪያ ሆኖን የሚኖር መልካም ስሙን አውርሶ ያለፈ እንደርሱ ላለ ደግና አስተዋይ አባት ያለ ስሙ ስም መሰጠቱ ቤተሰቡን በእጅጉ አሳዝኖታል።

ስምንተኛ <u>ሁሉም ነገር ከመንፈስ ቅዱስ በሚሰጥ አመርር እንደሚፈጸም ሆኖ የቀረበውን</u> በተመለከተ፤

በወንጌል እንደተጻፈው እግዚአብሔር ቃል ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም ለመስረታትና በደሙ ለቀደሳት ቤተ ክርስቲያኑ ፤ ከትንሣኤው በኋላ ከሃምሳኛው ቀን ጀምሮ መሪዋና ጠባቂዋ መጋቢዋም በዕለተ ጰራቅሊጦስ በእሳት አምሳል የወረደው መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱም አምላክ ቃል በሥጋ ተገልጦ ያስተማረውን ሃይማኖትና የገለጠውን እውነት (ምስጢር) ከክህደት፤ ከኑፋቄ ንጹሐን በሆኑ መምሕራን ዐድሮ በማስተማርና የተሰወረውን በመግለጥ ያንኑ ቢያፀና- ቢያቀና እንጂ በሌላ ስም ሌላ አላማ ያለው አዲስና እንግዳ ትምህርት አያስተምርም፤ አዲስ ሃይማኖትም አይመሰርትም። ይህንኑም መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል "... ወመጺኦ ጰራቅሊጦስ መንፈሰ ጽድቅ ውእቱ ይሜሕረክሙ ኩሎ ወያዜክረክሙ ኩሎ ዘነገርኩክሙ አነ፤እስመ እምዚአየ ይነሥእ ወይነግረክሙ ..." ማለት " ያ የዕውነት መንፈስ ጰራቅሊጦስ በመጣ ጊዜ እርሱ ኹሉን